# የሒደቱ ስኬታማነት

ቻላቸው /chebudie@yahoo.com/

ምርጫን ዴሞክራሲያዊ ከሚያስብሉት መስፈርቶች ቀዳሚው የምርጫው ሂደት ዴሞክራሲያዊነት እንጂ የአሸናፊው ፓርቲ ማንነት አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር ምርጫ የሚለካው በሂደቱ እንጂ በውጤቱ አይደለም። የሕዝብን ይሁንታ ያገኘ የመንግሥትን ሥልጣን ይረከባል እንጂ ማንም ስለፈለገና ስለተመኘ ወደ ሥልጣን ኮርቻ ሊፈናጠጥ አይችልም። በምርጫ የሚወዳደሩ አካላት ሁሉ የአሸናፊነት ፍላጐትና ስነልቦና ይዘው ወደ ውድድር ሲገቡ በዋናነት ዳኛው ህዝብ መሆኑን ተገንዝበው ውጤቱን በፀጋ የመቀበል ግዴታ ይኖርባቸዋል።

በህዝብ ድምፅ የሚገኝ ስልጣን ለመጨበጥ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች የራሳቸውን አጀንዳ ቀርፀው መንቀሳቀስ እንዳለ ሆኖ በተጨባጭ ለሀገሪቱ ውጤታማ ሊሆን የሚችል ፕሮግራም ይዞ መገኘት ግን ሌላ ነገር ነው። በህዝብ ለመገልገል ሳይሆን ሕዝብን የማገልገል ዓላማ ይዞ መነሳት ትልቅ ቁም ነገር ነው፡፡ ይህ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ወደ ሥልጣን የሚያመራውን መንገድ ነፃ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ከመራጮች ምዝገባ እስከ ድምፅ መስጠት አልፎም ውጤቱ እስኪገለፅ ያለውን የምርጫ ሂደት በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል። ከቅድመ ምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር አንስቶ እስከ አጠቃላይ ውጤቱ ድረስ ያሉት ሂደቶች በተገቢው መንገድ መካሄድ ለምርጫው ፍትሃዊነት የየራሳቸው አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

በ97ቱ ምርጫ ወቅትም ይሁን ዘንድሮ የሚካሄደው የምርጫ ቅስቀሳ ዴሞክራሲያዊነቱን ከጅምር ሂደቱ አንስቶ የሚፈታተኑ ጉዳዮች ከአንዳንድ አቅጣጫዎች ታይተዋል፡፡ እየታዩም ነው፡፡ ከምርጫ አስፈፃሚዎች እስከ ምርጫ ቦርድ ገለልተኝነትን መጠራጠርና አለመቀበል፣ በምርጫ ሂደቱ ላይ

የተከሰቱ ጥቃቅን ጉዳዮችን ሆን ተብለው ማግዘፍና ያልታሰረን ታሰረ ማለት፣ በተለያዩ የወንጀል ድርጊት ፈጽመው የታሰሩ ግለሰቦችን አባሎቻችን ታሰሩብን በማለት አቤቱታ ማቅረብ፣  ገና ባልተጣራ ጉዳይ ላይ አባላችን በኢህአዴግ /በገዥው/ ፓርቲ ሴራ ነው የተገደለው፣ የሕግና የዴሞክራሲ ተቋማትን ገለልተኝነት ማብጠልጠል  ወዘተ የሚሉት ይጠቀሳሉ። በተለይ በአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በኩል ይህ አይነቱ ሁኔታ በስፋት የተለመደ ተግባር ከሆነ ውሎ አድሯል። አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫ ክርክርና በምረጡኝ ቅስቀሳ ወቅት ዓላማና ፕሮግራማቸውን ከማስተዋወቅ ይልቅ በሀገሪቱ ያለውን የዴሞክራሲ ሂደት በጥቅሉ ማጣጣልን የተያያዙት ይመስላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ የዘንድሮው የምርጫ ሂደት ተቀዛቅዟል በማለት የተለያዩ ወገኖች አስተያየት ሲሰጡ ተደምጠዋል፡፡ ሆኖም ተቀዛቅዟል ያሉበትን ምክንያት ሊገልፁ ያለመቻል ሌላው ችግር ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በእኔ እይታ ግን መቀዛቀዝ ሳይሆን የሰከነና የሠለጠነ የምርጫ እንቅስቃሴ መታየት መጀመሩን ነው፡፡ የሰለጠነና የሰከነ ሲባል ተወዳዳሪ ፓርቲዎችም ሆነ መራጩ ህዝብ ካለፈው ምርጫ ብዙ ትምህርት ወስዶ የትኛው አዋጭ እንደሆነ በሚገባ እየተረዳ መጥቷል፡፡ ያለፈ ስህተትን መለስ ብሎ መመልከት ለወደፊት የሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ ዳግመኛ ችግር እንዳይፈጠር ማስተዋልን ይለግሳልና ፡፡

እንዲያው ወዳጆቼ፣ “አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ” ባትሉኝ በዚህ አመት ቀኑንና ፀሐፊውን ዘነጋሁት እንጂ “ምርጫ ሲደርስ የሚወለዱ ፓርቲዎች” በሚል ርዕስ የተፃፈ ፅሁፍ ማንበቤን አስታውሳለሁ፡፡ ምርጫ ሲደርስ ዕለቱን ተሰባስቦ ፓርቲ በመመስረት በአቋራጭ ወደ ሥልጣን ኮርቻ በመምጣት የግል ጥቅምን ማሳደጃ መንገድ እንዳይሆን ሥጋት አለኝ። ምርጫ ሲደርስ መምጫቸውና ስሪታቸው የማይታወቁ ፓርቲዎች እንደእንጉዳይ መፈልፈል የተለመደ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። በተለይ የምርጫ ቅስቀሳና ክርክሮች ሲደርሱ አይተናቸውና ሰምተናቸው የማናውቃቸው ፓርቲዎችንና ግለሰቦችን

ማየት መቻላችን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት በሀገራችን ምን ያህል እንደሰረፀ የሚያመለክት ቢሆንም አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች እዚህ ግባ የሚባል የፖለቲካ አማራጭ እንደሌላቸው መረዳት ችያለሁ። እውነተኛውን ከሀሰተኛው ለመለየት በሚያስቸግር መልኩ ቀልብ በሚስቡ ቃላት የተለጠጡ የሃሣብ ደሃ የሆኑ ወሬዎችን ማዳመጥ ዘንድሮም የተለመደ ሆኗል። አንዳንዶቹን ስመለከታቸው በማር የተለወሱ መርዞች ይመስሉኛል።

ፓርቲዎች ተወልደው በአጭር ጊዜ ለማደግ የማይቆፍሩት ጉድጓድ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ ይህ መጥፎ ድርጊት ነው ብዬ አይደለም። ነገር ግን ሀገርን የሚያህል ነገር ለመምራት አስተዋይነትንና ጥንቃቄን ይጠይቃል። "የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ" እንዳይሆን እኛ መራጮች ድምፃችንን ለማን መስጠት እንዳለብን አበክረን ልናስብበት ይገባል እላለሁ። በዘንድሮው የምርጫ ክርክርና የምርጫ ቅስቀሳዎች ወቅት የታዘብኩትም ይህንኑ ነው፡፡ ገዥው ፓርቲ በተግባር ውጤታማ የሆነባቸውን እና ያስመዘገባቸውን ውጤቶች በማሳየትና የዴሞክራሲ ሂደት በጊዜ የሚጎለብት እንጂ ዕለቱን የሚከሰት ነገር እንዳልሆነ ሲገልጽ  በተቃዋሚው ጐራ የተሰለፉት ፓርቲዎች ደግሞ ከሞላ ጐደል የኢህአዴግን የልማት እንቅስቃሴ በማጥላላትና በማጣጣል እንዲሁም አፍጠው አግጠው የሚታዩ እውነታዎችን በመካድ ምረጡኝ እንጂ የባህሩን፣ የየብሱንና የአየሩን በሙሉ ሳይቀር አደርግላችኋለሁ፤ በማለት ቃል መሐላ  መደርደሩን ተያይዘውታል፡፡

በ97 የተካሄዱ ክርክሮችን ሙሉ በሙሉ ለመከታተል ዕድሉ ነበረኝ፡፡ በዚህም የተወሰነ ግንዛቤ አለኝ ማለት እችላለሁ፡፡ እኔም የሚበጀኝን ለመምረጥ ያወጣኋትን ካርድ ሳላወላውል ለሚያስተዳድረኝ ለመስጠት በጥንቃቄ መመዘን መርጫለሁ፡፡ ማንን ከማን? በምንና እንዴት ላወዳድር? የሚሉትን ጥያቄዎች በሚገባ ለመመለስ ከ97ቱ ምርጫ ብዙ ተምሬአለሁ፡፡ ምክንያቱም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች መመረጥ ያለባቸው በሚያቀርቡት የአገር እድገት፣ ልማትና ብልፅግናን ሊያፋጥን በሚችል ፕሮግራምና ፖሊሲያቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል ብዬ እገምታለሁ፡፡

የ97ቱን ስህተት ላለመድገም መወሰድ ያለበት ጥንቃቄ ያለ ይመስለኛል። በወቅቱ በየምርጫ ጣቢያው ቀርበው የነበሩት ተወዳዳሪዎች የፓርቲዎቻቸውን አቋምና ስም ከማስተዋወቅ በዘለለ ግለሰቦቹ እነማን እንደሆኑ ምን ዓይነት ሥነ-ምግባር እንዳላቸው ከየት እንደመጡ እንኳን አይታወቁም ነበር። እስከአሁን በሚታየው ተጨባጭ ሁኔታም አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ፋክክር አንዱ የሌላውን ደካማ ጐን እየፈለገ የማጉላት እንጂ ፓርቲው በሚያራምደው የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ አተኩረዋል ለማለት አያስደፍርም። ዕጩ ተመራጮች በዋነኝነት በፓርቲያቸው ማንነት ላይ ስብዕናቸው የተመረኮዘ ቢሆንም በ97ቱ ምርጫ እንደታዘብነው በአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የቀረቡ ዕጩዎች በሥነ-ምግባራቸው በህብረተሰቡ ጥሩ ስም ያላቸው አልነበሩም። አማራጭና የተሻለ ነው ተብሎ የሚቀርብ አጀንዳ ምን እንደሆነና እንዴት በተግባር ሊተረጐም እንደሚችል ካልተብራራ ህዝቡን ለውሳኔ ማስቸገሩ አይቀርም፡፡ ለመቃወም ብቻ ተብሎም በተግባር ሊተረጐም የማይችል እና ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይመጣጠን ጉዳይ ጆሮ ኮርኳሪ የሆኑ ቃላቶች ተጠቅሞ ህዝብን ለማወናበድ መሞከር አንድ እርምጃ ሊያራምድ እንደማይችል ሁሉም የተረዳው ይመስለኛል፡፡

ከክርክሩ ይዘት ወጣ ልበልና እስኪ የ97ቱን ምርጫና የዘንድሮውን የምርጫ ሂደቶች በጥቂቱ ልዳስስ፡፡ ምርጫ 97 በመራጮች ተሳትፎ፣ በተወዳዳሪዎች ፉክክር፣ ምቹ የፖለቲካ ምህዳር በመፍጠር ወዘተ ረገድ ዓለምን ያስደነቀ እና በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሂደት እንደ እመርታ የሚቆጠር ነው። ይሁንና ወደዝርዝር ይዘቱ ጠለቅ ብለን ስንመለከት ጥላቻ፣ ስድብ፣ የእርስ በርስ ፍትጊያዎች የተስተናገዱበት፤ በቁጥር 15 /አስራ አምስት/ ያህል ክርክሮች የተስተናገዱበት፤ የተለያዩ ፓርቲዎች ተሰብስበውና ግንባር ፈጥረው ይሠሩ የነበሩበት ነገር ግን በጋራ ተስማምተው ያወጡት የስነምግባር ደንብ ያልነበረበት ምርጫ ነበር።

ምርጫ 2002 ከ97ቱ ምርጫ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነትም አለ። በዘንድሮው ምርጫ የሚካሔዱ ክርክሮች በቁጥር ከ97ቱ ቢለያይም የምርጫ ቅስቀሳው የተጀመረው ምርጫ ቦርድ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ነው። በአሁኑ ወቅት የሚወዳደሩ ፓርቲዎች እንደ 97ቱ በተለያየ ደረጃ ራሳቸውን ችለው እና ጥምረት ፈጥረው የመጡ ፓርቲዎች መሆናቸው የምርጫ ሥነ-ምግባር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ከአጉል ሰጣ ገባ የጸዳ ይሆናል ባይባልም፣ ከ97 የተሻለ መከባበር የታየበት ነው ማለት ይቻላል። በአጠቃላይ የቅስቀሳውና የክርክሩን ሂደት ደግሞ የሰከነና የሰለጠነ አካሄድ ነው ለማለት ያስደፍራል። በተጨማሪም እኛ መራጮችም ከአለፉት የምርጫ ሂደቶች በቂ ልምድ እንዳገኘን "ስንዴውን ከእንክርዳድ" የምንለይበት ወንፊት እንዳገኘን እረዳለሁ።

ሌላውና ዋናው ጉዳይ በዘንድሮ ምርጫ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በጋራ ተስማምተው ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ ተወያይተው አለም አቀፍ ይዘት ያለው የጋራ የምርጫ የስነምግባር ህግ ማውጣታቸው ነው፡፡ ይህ ህግ በምርጫ 97ቱ ወቅት አልነበረም፡፡ ግጭት ቀስቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ብሔርን፣ ጐሳን፣ ግለሰብን፣ ወዘተ.. አለአግባብ የሚያጥላሉ ንግግሮችን የሚያስወግድ ህግ ወጥቷል፡፡ በርካታ ቁም ነገሮችን የያዘ ህግ ስለሆነ ፓርቲዎች ሁሉ ቢተገብሩት ለሀገራችን የዴሞክራሲ ሂደት መዳበር አስተዋፅዖ አለው እላለሁ። በአራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተነሳሽነት የረቀቀና ከ60 በላይ የሚሆኑ ፓርቲዎች ተወያይተው ይሁንታ የሰጡት ከዚያም በተወካዮች ምክር ቤት ማሻሻያ ተደርጎበት የፀደቀውን የምርጫ ሥነ-ምግባር ህግ ማጣጣል ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም። ህጉ በገዥውም ሆነ በማንኛውም ተቃዋሚ ፓርቲ ላይ ተፈፃሚ የማይሆንበት ምንም ዓይነት መንገድ የለምና፡፡

ከዚህ ባለፈ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ማቋቋማቸው የግንቦት 2002ቱን ምርጫ ልዩ ያደርገዋል የሚል እምነት እንደሚፈጥር አያጠራጥርም፡፡ የጋራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ካለው ተግባርና ኃላፊነት አንደኛው በፓርቲዎች መካከል አቤቱታዎች ወይም አለመግባባቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ችግሮች ስለሚፈቱበት አሠራር አጠቃሎ መያዙ ነው፡፡

በዚህም መሠረት አቤቱታ አቅራቢ የፖለቲካ ፓርቲ "አዋጅ ተጥሷል" የሚል ቅሬታ ሲያቀርብ ምክር ቤቱ ከሚመለከታቸው ፓርቲዎች አጣሪ ቡድን በማውጣጣት ወይም ምክር ቤቱ የማጣራት ኃላፊነቱን ወስዶ ሊያጣራ ይችላል፡፡ ምክር ቤቱ በተለይ የስነምግባር ጥሰት አጋጥሟል ብሎ ያቀረበውን ፓርቲ እና አቤቱታ የቀረበበት ፓርቲ በጋራ ሆነው ችግሩን በመነጋገርና በስምምነት መፍትሔ የሚያገኙበት ዕድልም አጐናፅፏል፡፡ መጠላለፍ፣ መወነጃጀልና ወዳልሆነ አቅጣጫ እንዳይሄዱ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽ እንዳለው ይታመናል፡፡ በተግባርም ውጤቱን ማየት ተችሏል፡፡

መንግሥት ምርጫ 2002ን ነፃ ፍትሐዊ፣ ሰላማዊና በህዝብ ዘንድ ታማኝነት ያለው ለማድረግ ባለው ፅኑ እምነት በርካታ እርምጃቸውን እየወሰደ ነው። በ97ቱ ምርጫ ሰበብ የታሰሩ በርካቶች ከእስር እንዲፈቱ፤ የተዘጉ የተቃዋሚ ፓርቲ ጽህፈት ቤቶች እንዲከፈቱ ፍትሐዊ የቅስቀሳ የአየር ሰዓት ክፍፍል ወዘተ ተግባሮችን አከናውኗል። የስነ-ምግባር ደንቡ ከተፈረመ በኋላ የታሠሩ ሰዎችንና አንዳንድ ጥቃቅን ጉዳዮች እንዲስተካከሉ ማድረግ መቻሉን በተግባር እያየን ነው፡፡ ይህ ሁሉ የምርጫ የስነ-ምግባር ደንቡ ያስገኘው ውጤት ነው።

በተቃራኒው ያሉት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሀገሬው ዜጋ የምርጫ ስነምግባሩን ምንም ጠቀሜታ እንደሌለው፣ ቢፈርሙም ባይፈርሙም ለውጥ እንደማያስገኝ በመግለፅ በተቃራኒው የገንዘብ ምንጭ ለሆነው ዲያስፖራ ደግሞ በስነ-ምግባር ደንቡ መሠረት የተለያዩ ድሎችን በማግኘታችን በምርጫ መሳተፋችንን አትጥሉት የሚል መንታ አቋም ሲያንፀባርቁ ተደምጠዋል። ይህ አሳፋሪ ነው።

በአቋማቸው ፈጽሞ ሊስማሙና ሊተማመኑ የማይችሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በተለያየ መደለያና በሽምግልና ወደ አንድ ጥላ ሥር እንዲሰባሰቡ በማድረግ ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ ሥራ ያከናውናሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለኛል። አሁን በሀገራችን እያየን ያለነው እንዲህ ያለን ድርጊትን ነው "የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል" እንደሚባለው በትልልቅ

አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ተመሳሳይ አቋም የሌላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ጥላ ሥር ተሰባስበው ዛሬ የነገሩንን ነገ ሲሸሩት ውለው ሳያድሩም ሲፈረካከሱ አይተናል። ዛሬም ያንኑ ድርጊት እየተመለከትነው ነው። የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን በመደርደር የምርጫውን ሂደት ለማብጠልጠል መሞከር ለሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚፈይደው ነገር የለም።

ተገቢውን የውድድር ዝግጅት አለማድረግ እና የምርጫውን ሂደት ያለምክንያት ማብጠልጠል ለየቅል ናቸው። እኛ መራጮችም የምንታዘብበት ህሊና ስላለን ፍርዱን ለእኛ ብትተውልን መልካም ነው እላለሁ። በዚህ አካሄድ የውስጥ ችግርን ለመሸፈን መሻት አያዋጣም፡፡ ህዝቡ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድን ለሚመርጡ ኃይሎች ጆሮ የሚነሳበት እና በቃችሁ የሚልበት ቀን አሁን ይመስለኛል። ተከታይ ሲያጡና ገመናቸውን መሸፈን ሲቸግራቸው ተነጥለው መውጣታቸው አይቀርምና፡፡ እየተነጠሉም ይገኛሉና፡፡ ስለሆነም ፓርቲዎች ተፈጥረው እንደሚከስሙ ሁሉ መንግሥትም ይመጣል ይሄዳል፡፡ በማያቋርጥ ሂደት ላይ የሚቀጥለው ግን ሕዝብ ስለሆነ ካለፈው ታሪካችን የወረስነውን መጥፎ ጠባሳ ለታሪክ መዝጋቢዎች ትተን፣ አዲስ የመቻቻል፣ የመተሳሰብ፣ የመደጋገፍና የመደማመጥ ባህል ብናዳብር የሚበጅ ይመስለኛል፡፡

በ97ቱ ምርጫ ክንዋኔ ወቅት ለዓለም ያሳየነውን ድንቅ ዴሞክራሲያዊ ታሪክ ዛሬም በተሻለ አኳኋን መድገም እንችላለን ብሎ መናገር ይቀላል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባለፉት ዘመናት የኖርንበትን ህመም ደጋግመው እየጓጐጡ በህመም ውስጥ እንዳያኖሩንና ከዋሻው መጨረሻ ላይ የብርሃን ጭላንጭል መኖሩን እንዲያሳዩን የኢትዮጵያ ህዝብ ምኞት እንደሆነ አምናለሁ።

የእርስ በርስ ጥርጣሬ፣ ጥላቻና በቀል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጥንቱን ዓይነት ጤናማና ገንቢ ያልሆነ ግንኙነት መልሶ ለመድገም መመኘት ጊዜ ያለፈበት ከንቱ ቅዥት እንደሆነ በመገንዘብ ሀገራችንን ለላቀ ውጤት ለማብቃት ሁሉም ኃላፊነት አለበት፡፡ የምርጫን ጠቀሜታ ተረድተን

መብታችንን መጠቀም ይገባናል። የምርጫ ሒደቱን ለማደብዘዝና ለማኮሰስ ለሚነሱ ኃይሎች ጆሮ መስጠት የለብንም እላለሁ። ቸር እንሰንብት!